# የሕገ ወጥ እቃዎች መረጃ አሠጣጥ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያዎችን ስለመወሰን የወጣ መመሪያ

መ.ቁ. 15

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

81

## የሕገ ወጥ እቃዎች መረጃ አሠጣጥ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 15/2001

የሕገ ወጥ እቃዎችን እንቅስቃሴ የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ውስብስብ በመሆኑ እና እንቅስቃሴውንም በተሻለ ሁኔታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሕብረተሰቡን ተሣትፎ ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኮንትሮባንድ፣ የንግድ ማጭበርበር፣ የተከለከሉ ወይም ገደብ ከተደረገባቸው እቃዎች ጋር በተያያዘ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በይዘትም ሆነ በመጠን እየተበራከቱና እየተወሳሰቡ በመሄዳቸው በሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴ፣ በመንግስት ገቢ እንዲሁም በኀብረተሰቡ ደኅንነት ላይ አደጋ እያስከተሉ በመምጣታቸው ይህንን ሕገ ወጥ ድርጊት በተጠናከረ መልኩ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስልቶችን መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የኮንትሮባንድ እና ሌሎች የጉምሩክ ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ መረጃ ወሣኝ በመሆኑና ለዚህም አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ጠቋሚዎችና ያዦች ከተግባራቸው ጋር የተመጣጠነ ወሮታ ሊከፈላቸው የሚገባ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 78(3) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. *አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "የሕገ-ወጥ እቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝ እና የወሮታ ክፍያን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 15/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. *ትርጓሜ*

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1) "ሕገ ወጥ ዕቃ" ማለት የጉምሩክ ሕግን ወይም ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚያስፈጽማቸውን ሕጐች በመተላለፍ ተገቢው ቀረጥ እና ታክስ ያልተከፈለበት ወይም የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ወይም የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ነው፡፡
2) "ጥቆማ" ማለት ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል ስለ ሕገ-ወጥ ዕቃዎች የሚቀርብ መረጃ ነው፡፡
3) "ጠቋሚ" ማለት ስለ ሕገ-ወጥ ዕቃዎች እንቅስቃሴ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሕግ አስከባሪ አካል መረጃ የሚያቀርብ ሰው ሲሆን የባለስልጣኑን ሠራተኞች አይጨምርም፡፡
4) "ያዥ" ማለት ሕገ-ወጥ ዕቃውን ይዞ ለባለሥልጣኑ ገቢ ያደረገው ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ነው፡፡
5) "ሠራተኛ" ማለት በባለሥልጣኑ መ/ቤት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ነው፡፡
6) "ተባባሪ" እና "ድጋፍ ሰጪ" ማለት ሕገ ወጡ ዕቃ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲያዝ ለማድረግ የተሳተፈ ማንኛውም ሰው ነው፣
7) "የወሮታ ክፍያ" ማለት በጥቆማ ወይም በጥቆማ ሠጪ ሕገ ወጥ ዕቃ ተይዞ በሕግ ተወርሶ ለባለሥልጣኑ ገቢ ሲሆን ወይም በማንኛውም መልኩ ሲወገድ ይህንን ለጠቆሙ ወይም ለያዙ ወይም ለተባበሩ ሰዎች የሚሰጥ ክፍያ ነው፡፡

83

8) "ሕግ አስከባሪ" ማለት በሕግ ማስከበር ተግባር ላይ የተሠማራ የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት አካል የሆነ የታጠቀ ወይም ያልታጠቀ ኃይል ወይም ሠራዊት ነው፡፡

9) "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

10) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሕገ-ወጥ ዕቃዎች ላይ የሚቀርቡ ጥቆማዎች አቀራረብ፣ አያያዝ፣ የተያዙ እቃዎች ለባሥልጣኑ ገቢ ስለሚሆኑበት ሁኔታ እና በወሮታ አከፋፈል ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለጥቆማ

### 4. መሠረቱ

በአገሪቱ የጉምሩክ ክልል በየትኛውም ሥፍራ ሕገ-ወጥ ዕቃ መኖሩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ወዲያውኑ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

### 5. ጥቆማ የማይቀርብባቸው ሁኔታዎች

1) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የሚከተሉት ሁኔታዎች ጥቆማ የማይቀርብባቸው ናቸው፡-

ሀ/ በሕዝብ የሚታወቁ ሕገ-ወጥ እቃዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች፣

ለ/ ቀደም ሲል በጠቋሚ መረጃ የቀረበባቸው፣

ሐ/ በአሳማኝ እና በበቂ ማስረጃ እና መረጃ ያልተደገፉ ጥቆማዎች፡፡

2) ባለስልጣኑ ከጠቋሚው የቀረበለትን መረጃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ካልተቀበለው ወዲያውኑ ለጠቋሚው በጽሑፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 6. *የጥቆማ አቀባበል*

ባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪው አካል ሕገ ወጥ እቃ ስለመኖሩ የቀረበለትን መረጃ የሚቀበለው፡-

ሀ/ ከጠቋሚው በስተቀር በሌላ በማናቸውም ዘዴ መረጃውን ማግኘት የማይቻል ከሆነ፣ ወይም

ለ/ በዚህ አንቀጽ በፊደል "ሀ" የተጠቀሰው ቢኖርም የሕገ ወጥ እቃዎች መረጃ ቀደም ሲል በባለሥልጣኑ ወይም በሕግ አስከባሪው አካል የሚታወቅ ቢሆንም የቀረበው መረጃ እቃው የሚገኝበትን ትክክለኛ ስፍራ የሚያመለክት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## 7. *የጥቆማ አቀራረብ ዘዴዎች*

ማንኛውም ጠቋሚ ለባለሥልጣኑ የመረጃ ንዑስ የሥራ ሂደት ጥቆማውን በጽሑፍ፣ በቃል፣ በስልክ፣ በፋክስ ወይም በሌሎች ማናቸውም የመገናኛ ዘዴዎች ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 8. *የጥቆማ አመዘጋገብ*

1) ማንኛውም ጥቆማ በጥቆማ መቀበያ ቅጽ ላይ እንደቅደም ተከተሉ በጥንቃቄ ይሞላል፤ ጥቆማውን ላቀረበው ሰውም አንዱ ቅጂ ይሰጣል፡፡

2) ለሕግ አስከባሪ የቀረበ ጥቆማ በ48 ሰዓት ውስጥ ባሉት የመገናኛ ዘዴዎች በአቅራቢያው ለሚገኘው የባለሥልጣኑ መ/ቤት ይተላለፋል፣ በንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረትም ይመዘገባል፡፡

85

## 9. የጥቆማ ምስጢራዊነት

1) በሕገ-ወጥ ዕቃዎች ላይ የሚደረግ ማንኛውም ጥቆማ እና የጠቋሚው ማንነት አግባብነት ካለው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ኃላፊ በስተቀር ለማንም ሰው ወይም አካል ምስጢራዊ ሆኖ ይጠበቃል፡፡
2) ባለሥልጣኑ የጠቋሚውን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማናቸውም የመረጃ ብክነት እንዳይኖር ከፍተኛ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማንኛውም ጥቆማ አስገዳጅ እና አሳማኝ ሕጋዊ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ተቋማዊ ይሆናል፡፡
4) ማንኛውም የባለስልጣኑ ሠራተኛ የተቀበለውን ጥቆማ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ላይ ከተደነገገው ውጪ መረጃውን በጽሑፍ፣ በቃል ወይም በሌላ በማናቸውም ዘዴ ለማንኛውም ሰው አሳልፎ የሰጠ ወይም ምስጢራዊነቱን ያባከነ እንደሆነ በወንጀል ሕግ መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲሲፒሊን እንዲከሰስ ይደረጋል፡፡

## 10. የጠቋሚ የምስጢር መለያ

ባለሥልጣኑ ማንኛውንም ጠቋሚ የሚለይበት እንዲሁም ከጠቋሚው ጋር ለሚኖረው ማንኛውም ግንኙነት የተለየ የምስጢር መለያ ቁጥር ወይም ስም ለእያንዳንዱ ጠቋሚ ይሰጣል፡፡

## 11. ስለጥቆማ ቅጽ፣ ይዘት፣ አቀማመጥ እና ስርጭት

በሕገ-ወጥ ዕቃዎች ላይ የሚቀርቡ የጥቆማ መረጃዎች መቀበያ እና መከታተያ ማኅደሮች፣ ቅጾች፣ የቅጾቹ ይዘት ዝርዝር እና ብዛት፣ አያያዝ እና አጠባበቅ የመረጃ ንዑስ የሥራ ሂደትን ተግባር ለመፈጸም በተዘጋጀው ማንዋል መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

86

## 12. በባለሥልጣኑ ስለሚመለመሉ ጠቋሚዎች

የሕገ-ወጥ ዕቃ ጠቋሚ አመላመል፣ ሥነ ምግባር፣ ምስጢር አጠባበቅ፣ ሥነ ሥርዓት እና የመረጃ ጥበቃ ሥልቶች በተዘጋጀው ማንዋል መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

# ክፍል ሶስት

# ስለ ሕገ ወጥ እቃዎች አያያዝ

## 13. ሕገ-ወጥ እቃን መያዝና ማስረከብ

1) ባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪው ሕገ ወጥ እቃ ስለመኖሩ ጥቆማ እንደቀረበለት እቃውን ወዲያውኑ ይይዛል።
2) ዕቃው በሕግ አስከባሪው የተያዘ እንደሆነ ባለበት ሁኔታ ተመዝግቦ በ24 ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እንዲተላለፍ እና ርክክብ እንዲፈፀም ይደረጋል።
3) ባለሥልጣኑ የተያዙትን ዕቃዎች በጥንቃቄ መዝግቦ ይረከባል፤ ለያዘው እና ለተረከበው ዕቃ ለሚመለከተው ሰው ወይም ክፍል ሕጋዊ ማስረጃ ይሰጣል።

## 14. የተያዙ ዕቃዎች አቀማመጥ

1) የተያዙ ዕቃዎች ወዲያውኑ ወደ ባለሥልጣኑ መጋዘን ገቢ ተደርገው ተገቢው አጠባበቅ እና ክትትል ይደረግባቸዋል።
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የተያዘው እቃ በጉምሩክ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች መሠረት ለአቀማመጥ ወይም ለአጠባበቅ የማይመች፣ የሚበላሽ ወይም ለሕዝብ ጤና እና ደህንነት አደገኛ ሆኖ ከተገኘ በፎቶግራፍ ወይም በቪዲዮ ምስሉ እንዲቀረጽ ተደርጐ የሚመለከተው ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት እንዲረከበው ወይም እንዲሸጥ ወይም እንዲወገድ ይደረጋል።

## 15. በተያዘ ዕቃ ላይ እንዳይፈፀም የተከለከለ ተግባር

1) ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ወይም ሕግ አስከባሪ የተያዘን ወይም በቁጥጥር ሥር የዋለን ዕቃ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲውል ማድረግ፣ መሸጥ፣ መለወጥ፣ ማውደም፣ መቀነስ፣ እሽጉ እንዲፈታ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ፣ ለአያያዝ እና ለአቀማመጥ እንዳይመች ማድረግ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ሕገ-ወጥ ተግባራትን መፈፀም የለበትም፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘረውን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሞ የተገኘ የባለሥልጣኑ ወይም ሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኛ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡

# ክፍል አራት
# የወሮታ ክፍያ እና አፈፃፀም

## 16. መሠረቱ

1) ለባለሥልጣኑ በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ያለምንም ጥቆማ ሕገወጥ ዕቃ በተያዘ ጠቋሚው፣ያዡ፣ ትብብር እና ድጋፍ ያደረጉት በሙሉ በዚህ መመሪያ መሠረት የወሮታ ክፍያ ይከፈላቸዋል፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሠረት የወሮታ ክፍያ የሚከፈለው ለባለሥልጣኑ ገቢ የሆነው ሕገ ወጥ ዕቃ በሽያጭ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ እንዲተላለፍ ከተደረገ ወይም እንዲወገድ ከተደረገ ወይም ለተያዘው ዕቃ ቀረጥና ታክሱ ተከፍሎ እንዲወጣ ከተደረገ ነው፡፡
3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(1) መሠረት የጠቋሚነት ማስረጃ የተሰጠው ሰው የክፍያ ጥያቄ በሚያቀርብበት ወቅት የማስረጃውን ዋና ቅጂ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 17. ሕገ-ወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ ሆኗል ስለሚባልበት ሁኔታ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል ሕገ ወጥ ዕቃ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንደተደረገ የሚቆጠረው፡-

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Revenues and Customs Authority

1) የተከለከለ ዕቃ ከሆነ በባለሥልጣኑ እንደተያዘ ወይም ባለሥልጣኑ እንደተረከበው፣ ወይም

2) ባለቤቱ ያልታወቀ ሕገ ወጥ ዕቃ ተይዞ በአዋጁ መሠረት የዕቃው ባለቤት ነኝ ባይ እንዲቀርብ በማስታወቂያ ተጠርቶ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ሳይቀርብ ከቀረ፣ ወይም

3) በሕገ-ወጡ ዕቃ ባለቤት፣ በግብረ አበሮቹ እና/ወይም በተባባሪዎቹ ላይ ባሉበትም ሆነ በሌሉበት በቀረበባቸው የወንጀል ክስ መሠረት ሥልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት በዕቃው ላይ የውርስ ውሣኔ ሲሰጥ ወይም ተከሣሹ ፍርድ ቤት ባለመቅረቡ ምክንያት ክስ የማቅረብ መብት ተጠብቆ በተዘጋ ክስ ላይ ፍርድ ቤት ሕገ-ወጥ ዕቃው ተሸጦ ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲሆን ትእዛዝ ሲሰጥ፣ ወይም ባለሥልጣኑ ህገ ወጡ እቃ በአስተዳደራዊ ውሣኔ አስፈላጊውን ክፍያ ተከፍሎ እንዲወጣ ሲወስን፤ወይም

4) የሕገ-ወጥ ዕቃው ባለቤት በአስተዳደራዊ ውሣኔ ሕገ-ወጡ ዕቃ እንዲወረስ ስምምነቱን በፊርማው ሲያረጋግጥ ነው።

## 18. የወሮታ ክፍያ መጠን

1) የተያዘው ዕቃ ሲሸጥ የወሮታ ክፍያው መጠን ከሽያጩ ዋጋ ላይ፡-

ሀ. ለጠቋሚው 40%፣

ለ. ለያዥ፣ ድጋፍ እና ትብብር ለሚያደርጉ 30%፣

ሐ. ሕገ-ወጡ ዕቃ የተያዘው ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ሠራተኞች ተሣትፎ ውጪ በክልል መስተዳድር አካላት ወይም በመከላከያ ሰራዊት ከሆነ ለተቋሙ 100% የወሮታ ክፍያ ይከፈላል፤

መ. ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) አፈፃፀም ለተቋሙ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለተቋሙ ከሚከፈለው 100% ክፍያ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጎ ለጠቋሚው ይከፈላል።

89

2) በቀረጥ ነፃ ወደ አገር ገብተው መብቱ በሌላቸው ግለሰቦች ይዞታ ሥር የተያዘን እቃ በተመለከተ የሚከፈለው የወሮታ መጠን ለእቃው ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ ላይ፡-

ሀ/ ለጠቋሚው 10%፣

ለ/ ለያዥ፣ ~~ድጋፍ እና ትብብር ላደረጉ~~ 5%፣

ሐ/ እቃው የተያዘው ከባለሥልጣኑ መ/ቤት ሠራተኞች ተሣትፎ ውጭ በክልል መስተዳድር አካላት ወይም በመከላከያ ሠራዊት ከሆነ ለተቋሙ 50% የወሮታ ክፍያ ይከፈላል፡፡

መ/ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) አፈፃፀም ለተቋሙ ጥቆማ ያቀረበው ግለሰብ ከሆነ ለተቋሙ ከሚከፈለው 50% ክፍያ ላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ሀ) የተመለከተው ተቀናሽ ተደርጐ ለጠቋሚው ይከፈላል፡፡

ሠ/ የወሮታ ክፍያው መጠን በማንኛውም መልኩ ለቀረጥ ከተከፈለው 50% አይበልጥም፣

3) ሽያጭ ላይ የማይውሉ ሕገ-ወጥ እቃዎች የወሮታ ክፍያ መጠን

የተያዘው እቃ ቅርሳ ቅርስ፣ በሕግ የተከለከሉ የዱር እንስሳት ተዋጽኦዎች፣ የጦር መሣሪያ፣ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ እና አደገኛ ወይም መርዛማ ኬሚካል እና ዝቃጮች፣ ትምባሆ፣ መድሀኒቶች፣ ልባሽ ጨርቅ እና ሌሎች በሽያጭ ሊወገዱ የማይችሉ እቃዎች የሆኑ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለጠቋሚ፣ ያዥ፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ ሰዎች እንደሚከተለው ክፍያ ይፈፀማል፡፡

ሀ/ ልባሽ ጨርቅ ከሆነ በኪሎ ብር 10 ሆኖ ለጠቋሚ፣ ለያዥ፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ በሙሉ እኩል ይከፋፈላል፡፡

ለ/ በሚመለከተው መስሪያ ቤት ዋጋ የወጣላቸው ከሆኑ የዚህኑ ዋጋ ለጠቋሚ 20%፣ ለያዥ፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ 15%፣

ሐ/ የገበያ ዋጋ ሊወጣላቸው የማይችሉ ከሆኑ ባለስልጣኑ በማስዩመጡ ከ3 አባላት ባላነሱ የቡድን አባላት እንደየ እቃው ባህሪ እየተጣራ ለጠቋሚ 10%፣ ለያዥ፣ ድጋፍና ትብብር ላደረጉ 5% ይከፈላል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

4) በጠቋሚ፣ በያዥ፣ በድጋፍና ትብብር ማድረግ ሂደት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ ከቀረቡ በጋራ ይመዘገባሉ፤ የሚከፈለው የወሮታ ክፍያም በጋራ ይፈፀምላቸዋል፤ ሆኖም በተናጠል ከቀረቡ እንደየድርሻቸው ክፍያ ይፈፀማል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 19. የይርጋ ጊዜ

1) የወሮታ ክፍያው መፈጸም ካለበት ጊዜ ጀምሮ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የክፍያ ጥያቄ ካልቀረበ መብቱ በይርጋ ይታገዳል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የክፍያ ጥያቄው የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመሆኑ አሳማኝ ማስረጃ ከቀረበለት ባለስልጣኑ የጊዜ ገደቡን ለተጨማሪ 6 ወራት ሊያራዝም ይችላል፡፡

### 20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት የነበሩ ጉዳዮች በሙሉ ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ በነበረው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### 21. የተሻሩ መመሪያዎች

የሕገ ወጥ እቃዎች መረጃ አሰጣጥ፣ አያያዝና የወሮታ ክፍያዎችን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 39/1999፣ 49/2000 እንዲሁም በቁጥር ዘ10/አ17/19 ጥቅምት 9 ቀን 1999 ዓ.ም. በጉምሩክ ባለስልጣን የወጣው ዝርዝር የወሮታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

### 22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 1 ቀን 2001 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

91